ETHIOPIAN COMMUNITY IN MINNESOTA

የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሚኒሶታ

# ለኢትዮጵያ ማኅበረሰብ አባላት
## የተሰጠ መግለጫ

ቀን፡ ጥር 26/2011

ከጥቂት ወራት ወዲህ ጀምሮ ከመተዳደሪያ ደንባችን ጋር በተጋጩ የአሠራር ችግሮች የተነሣ በማኅበራችን አመራር አባላት መካከል አለመግባባት በመፈጠሩና ይህን የሚያንፀባርቁ መልእክቶች በሶሻል ሚዲያ መተላለፋቸው የኅብረተሰባችንን ስሜት መጉዳታቸው ይታወቃል።

ሆኖም ጥር 18 ቀን 2011 ዓም (01/26/2019) ሴንትፖል በሚገኘው የማኅበረሰቡ ጽ/ቤት በኢትዮጵያ ማኅበረሰብ አጠናካሪ ግብረ-ኃይል አስተባባሪነት፥ የተለያዩ የሃይማኖት አባቶችና በሕዝብ የተጠቆሙ ሽማግሌዎች በተገኙበት፥ በማኅበረሰቡ አመራር መካከል የእርስ በእርስ ውይይት ከተደረገ በኋላ፥ የሃይማኖት መሪዎች ባደረጉት ማግባባትና በተለይም ብፁዕ አቡነ ኢዮስጣጤዎስ (ዶክተር) የሚኒሶታና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ ባደረጉት የእርቅ ሥነሥርዓት፥ በአመራሩ የተወሰዱ እርምጃዎች የተነሱ ስለሆነ፤ የማኅበረሰቡ የሥራ አመራር አካላትም አባቶችን በማክበር የዕርቁን ሥነሥርዓት ተቀብለን በአንድ ላይ ተባብረን ለመሥራት ተስማምተናል።

በተቻለን መጠን ሥርዓትንና ወገን ለመከተል ባደረግነው ጥረት ችግሩን ለመፍታት ጊዜ በመውሰዱ ማኅበረሰባችንን ልባዊ ይቅርታ እየጠየቅን፤ በተፈጠረው እርቀ- ሰላም መሠረት መጪውን የአደዋ የድል መታሰቢያ በዓል በደመቀ ሁኔታ ለማክበር ከግብረ-ኃይሉ ጋር በጋራ አስፈላጊ ዝግጅቶችን ለማድረግ መወሰናችንን በደስታ እንገልፃለን። ከበአሉ በኋላ የማኅበረሰቡ አመራር በአጭር ጊዜ ውስጥ ጠቅላላ የአባላት ዓመታዊ ጉባኤ ይጠራል፤ ጉባኤው ዓመታዊ ርፖርት ከሰማ በኋላ በሥራ አፈጻጸምና በጋራ ማዕከል ላይ እንደሚያተኩር በሚጠበቅ ዕቅድ ላይ ውይይት ይደረጋል።

"ኢትዮጵያዊነት ክብር ነው"

በሚኒሶታ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ

1821 University Ave. W Suite No 233 St. Paul MN 55104

Tel: 651-645-9668 web: www.ethiopiamn.org Email: ecmonemn@gmail.com